# ሳሙኤል አለማየሁ

ከጌትነት ኖርዌ

የኢምፔሪያሊዝሙ ምች
የብዙሃኑ መብት ተሟጋች
የምዝብሩ ጠበቃ የጠባቦች የጎን ውጋት
የቁርጥ ቀኑ ልጅ የፋሽስቶች መርገምት
እንዴት ነው ዕረፍቱ
የሰልስት ዓመቱ
ለእኛማ ዛሬ ብትኖርልን
ስንቱን በቀየስክልን
ስንቱንስ ከሃዲ ባሳፈርክልን
ይሄውልህ ሳሙኤል
የእኛው ጠዊል
የትግል መሐንዲሱ አባ ገድል
ከጉድጓድ እሥርቤቱ
ጓዶችህ እየማቀቁ ያሉቱ
ጊዜ በሰጠው ቅል ተሰብረው
ድምጻቸው እንደጠፋ ነው
አገርህም ጠቢያ ተንቃ
ባላዋቂ ሳሚዎች ንፍጥ ተለቅልቃ
በቤት ፍርሻ ድግስ ሞቃ
ጨቅይታ ተጨማልቃ
እያዳመጠች የልጆቿን ሲቃ
ጣር በዝበቶባት ትጣራለች
እናንተን አምጡ እያለች